# በምርመራ ወቅት ለፖሊስ የተሰጠ የእምት ቃል በማስረጃነት ስለሚወሰድበት አግባብ

በሰለሞን ተገኘወርቅ*

***<u>አጽርኦተ-ይዘት</u>***

*በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ የተጠርጣሪ የእምነት ቃል እንደ ሌሎች ማስረጃዎች አግባብነትና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ በእርግጥ ማስረጃው ተቀባይነት የሚኖረው ተጠርጣሪው በራሱ ፍላጎት ያለምንም ተጽዕኖ የሰጠው የእምነት ቃል ሲሆን ነው፡፡ በተጨማሪም የእምነት ቃሉ የተገኘው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ ለተጠርጣሪ የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ተፈጻሚ ሆነው የሰጠው ቃል ሲሆን ነው፡፡ እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ዓላማ ተደርገው የተቀመጡበት ዋናው ምክንያት ተጠርጣሪው አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገባ ለመከላከል ያግዛሉ በሚል እምነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተግባር መርማሪ ፖሊሶች ቃል በሚቀበሉበት ወቅት እነዚህን ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የማያከብሩበት ጊዜ ያጋጥማል፡፡ ታዲያ ተጠርጣሪው በፍርድ ቤት በሚከራከርበት ወቅት በህጉ የተቀመጡት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (መብቶቼ) ሳይነገሩኝ የሰጠሁት የእምነት ቃል ስለሆነ በማስረጃ ሊያዝብኝ አይገባም የሚል ክርክር ቢያቀርብ ፍርድ ቤቶች ምን መወሰን አለባቸው የሚለው አከራካሪ ሲሆን ይታያል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉም ሆነ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) ህገ መንግስት የተጠርጣሪው መብቶች ሳይገለጹ የሰጠው የእምነት ቃል ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መልስ ስላልሰጡ ነው፡፡ ህጉ በፈጠረው ክፍተት ምክንያት በባለሙያዎች ዘንድ ሁለት ዓይነት አረዳድና አሰራር እንዲኖር ምክንያት ሆኗል፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ* ***በፊት ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑና የተናገረው ነገር እንደ ማስረጃ በፍርድ ቤት እንደሚወሰድ ሳይነገረው የሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ውድቅ ሊደረግ ይገባል*** *በማለት ይከራከራሉ፡፡ በሌላ በኩል ይህንን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ለተጠርጣሪው መገለጽ እንዳለባቸው በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይፈጸም የተሰጠ የእምነት ቃል ቢኖር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ውጤቱ ምን መሆን እንዳለበት ያስቀመጠው ነገር* ***ስለሌለ ማስረጃውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት ስለሌለ ማስረጃውን መቀበል ይገባል በሚል በዚሁ አግባብ ሲሰሩ ይታያል፡፡*** *እንደጸሀፊው እምነት ከሆነ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የተቀመጡበትና በወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ያላቸው ታሪካዊ እድገትም ሲታይ ተጠርጣሪው የሚሰጠው የእምነት ቃል ያለምንም ተጽዕኖ በነጻ ፈቃዱ እንዲሰጥ ለማስቻል በመሆኑ ይህ መብት ሳይከበር የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይት ሊኖረው አይገባም፡፡*

---

* (LLB, LLM በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት የአዲስ አበባ ቋሚ ምድብ ዐቃቤ ህግ (ከዚህ በፊት በኢንስቲትዩቱ አሰልጣኝና ተመራማሪ የነበረ))፡፡

## 1. ስለእምነት ቃል አንዳንድ ነጥቦች

የአንድ ሀገር የወንጀል ፍትህ ስርዓት ዋና ግብ ተደርጎ የሚወሰደው በሀገርና በህበረተሰብ ላይ ወንጀል እንዳይፈጸም አስቀድሞ መከላከል ሲሆን መከላከሉን አልፎ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ ጠንካራ የምርመራና የማስረጃ አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ወንጀለኞችን ጥፋተኛ ለማስባል የሚያስችል ማስረጃ በማቅረብ አጥፊዎች ተገቢ የሆነ ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡[1] የወንጀል ጉዳይን ለማስረዳት የተለያዩ የማስረጃ ዓይነቶች እንዳሉ ከተለያዩ የማስረጃ ህግ አስተምህሮቶች ማየት ይቻላል፡፡[2] ከእነዚህም ውስጥ የሰው ምስክርነት፣ የሰነድ ማስረጃ፣ የኤግዚቪት ማስረጃ፣ የቴክኒክ ማስረጃ፣ የተጠርጣሪው /የተከሳሽ/ የእምነት ቃልና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡[3] የተጠርጣሪ የእምነት ቃል በሀገራችንና በሌሎች ሀገራት የማስረጃ ህግ ወይም የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ አግባብነትና ተቀባይነት ካላቸው ማስረጃዎች አንዱ በመሆኑ በወንጀል ምርመራ ወቅት የተጠርጣሪን ቃል የመቀበል ስራ ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡[4] በወንጀል ምርመራ ሂደት የተጠርጣሪን የእምነት ክህደት ቃል መቀበል የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ያለምንም ተጽዕኖ በራሱ ፍላጎት ወንጀል በመፈጸሙ ምክንያት በመጸጸት በአንደበቱ ስለወንጀል አፈጻጸሙ በዝርዝር የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ስለሚችልና የሚሰጠውም የእምነት ቃል ወንጀሉን ለማስረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ነው፡፡[5] በሌላ በኩል ተጠርጣሪው በሚሰጠው የእምነት ቃል መነሻነት ሌሎች ግዙፍና ግዙፍነት የሌላቸውን ማስረጃዎች ለማሰባሰብ መርማሪ ፖሊሶች በእጅጉ ስለሚጠቀሙበት ነው፡፡ ለምሳሌ ተጠርጣሪው በእምነት ቃሉ ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሳው ምክንያት ምን እንደነበረ?፣ ወንጀሉን መቼ እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉን እንዴት እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉ የት እንደተፈጸመ?፣ ወንጀሉን በምን ዓይነት መሳሪያ እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉን ሲፈጽም ግብረ አበሮች ከነበሩት ግብረ አበሮቹ እነማን እንደሆኑና አድራሻቸው የት እንደሆነ ሊጠቁም ይችላል፡፡[6] ከእዚህም ሌላ ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ ወንጀል የተፈጸመው በንብረት ወይም በእንስሳ ላይ ከሆነ ንብረቱ /እንስሳው/ የት እንደሚገኝ፣ ወንጀል የፈጸመበት መሳሪያ የት

---

[1] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ (1996 ዓ.ም) የወንጀል ህጉ ዓላማ በሚለው ስር የተቀመጠው እና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣ (2003 ዓ.ም)

[2] John Henry, Evidence in trials at common law, 3rd ed. V. 3, Boston Little brown and Company, 1940, ገጽ 248-250

[3] ዝኒ ከማሁ

[4] በኢትዮጵያ፣ በእንግሊዝ፣ በአሜሪካ፣ በህንድና በሌሎች አገሮች የማስረጃና የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ ተጠርጣሪ ለመርማሪ ፖሊስ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ የሚወሰድ መሆኑን በየሀገራቱ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎናችና የማስረጃ ህጎች ተካቶ ይገኛል፡፡

[5] 'Confessions', American Jurisprudence, 2nd ed., V. 29, (1967) ገጽ 276

[6] ዝኒ ከማሁ

እንደሚገኝ፣ የወንጀሉ ሰለባ የሆነው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ተጎጂው ወይም የተጎጂው አስከሬን የት እንደሚገኝ፣ ተጎጂው በወቅቱ ለብሶት የነበረው ልብስ ወይም ሌላ በእጁ የነበረ ማናቸውም ነገር የት እንደሚገኝ በዝርዝር የሚገልጽበት አጋጣሚ ስለሚኖር የተጠርጣሪውን ቃል በመጠቀም ለተጨማሪ ምርመራ በር ከፋች ስለሚሆን ነው፡፡[7] የተጠርጣሪን የእምነት ቃል የመቀበል ዓላማ እነዚህና ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆን አንድ ተጠርጣሪ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ ተቀባይነት እንዲያገኝና እንደ ማስረጃ ተወስዶ ከማስረጃ ምዘና ውስጥ እንዲገባ ማስረጃው የተገኘው ከማናቸውም ዓይነት ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ የተሰጠና ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በሙሉ ፍላጎቱና ነጻ ፈቃዱ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡[8] የቃል መቀበል ሂደት በባህሪው መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪው ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ የሚፈልግበት ተግባር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት መርማሪ ፖሊስ በተጠርጣሪው ሰብዓዊ መብት ላይ ጥሰት ሊፈጽም የሚችልበት እድል ይኖራል፡፡ ይህ እንዳይፈጸም ለማድረግ የሚያግዙ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards /protection methods) በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት እና በሌሎችም ሰነዶች ላይ ተገልጸ ይገኛል፡፡[9] እነዚህ ጥበቃዎች ምንድን ናቸው ብለን ብንጠይቅ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብበት መሆኑ ሊነገረው የሚገባ መሆኑ፣ ጠበቃ የማማከር መብት ያለው መሆኑ፣ የሰጠው ቃል ሁሉ መመዝገብ የሚገባው ስለመሆኑና ቃሉን ከሰጠ በኋላ በሰጠው ቃል ላይ ከመፈረሙ በፊት የሰጠውን ቃል እንዲያነብ እንዲደረግ ወይም እንዲነበብለት መደረግ ያለበት መሆኑን የሚገልጹ መብቶች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡[10]

ከላይ እንደተመለከትነው ተጠርጣሪው የሚሰጠው የእምነት ቃል በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖረው ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው **በራሱ ነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፈቃደኝነት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ** ነው፡፡[11] ምክንያቱም የእምነት ቃሉ የተገኘው በነጻ

---

7 ዝኒ ከማሁ

8 Richard A. እና Leo Richard J. Consequences of False Confessions: Deprivations of Liberty and Miscarriages of Justice in the Age of Psychological Interrogation, **Journal of Criminal Law and Criminology** Volume 88, በ www.campbellcollaboration.org ላይ ይገኛል፣ ገጽ 431-432፣ ሚያዚያ 26/2011 ዓ.ም የተወሰደ እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(5) ስር እንደተገለጸው በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው ተደንግጓል፡፡

9 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(2)፣ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 27(2)

10 ዝኒ ከማሁ

11 Saul M. Kassin Æ Steven A. Drizin Æ Thomas Grisso, Police-Induced confessions, risk factors and recommendations, በ www.campbellcollaboration.org, የሚገኝ ገጽ 3፣ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም ተወሰደ

ፍላጎትና ህጉ ያስቀመጠውን ስርዓት ተከትሎ ባልሆነ ጊዜ ማህበረሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት ያጣል፤ የተጠርጣሪውን ሰብዓዊና መሰረታዊ መብቶች ይጥሳል።[12] ለምሳሌ ያክል የተወሰኑ ጉዳዮችን ወስደን ብንመለከት በፖሊስ የሚወሰዱ የተጠርጣሪ የእምነት ቃሎች ከተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት ውጭ በሆነ መንገድ የተሰጠ የእምነት ቃል ሀሰት ሊሆን ስለሚችል በሀሰተኛ ማስረጃ መሰረት ንጹሀን ያለጥፋታቸው አላግባብ ሊፈረድባቸው ይችላል፤ ትክክለኛ ወንጀል ፈጻሚዎችም ከፍትህ ተጠያቂነት ሊያመልጡ ይችላሉ፤ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ በወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ላይ ያለው እምነት ሊሸረሸር ይችላል።[13] በሌላ በኩል አንድ ተጠርጣሪ ባልፈጸመው ወንጀል የእምነት ቃሉን በተለያዩ አላማ (motive) ሊሰጥ የሚችልበት እድል ይኖራል።[14] ይሄውም አንድም የእምነት ቃሉ የተሰጠው በመርማሪው በኩል በሚደረጉ የማስገደድ፣ የማባበል ወይም ከሌሎች የአካልና የስነ-ልቦና ጫናዎች ለመላቀቅ ሲባል ሊያምን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ተጠርጣሪው ከራሱ ወይም ከቅርብ ቤተሰቡ ከሚመነጭ ግፊት ቤተሰቡ ወይም የሚወደው ሰው እንዳይታሰርበት ለማድረግ በማሰብ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ደም መላሽ ወይም ጀብደኛ ሆኖ ለመታየት በመፈለግ፣ በገንዘብ በመገዛት እና በሌሎችም ምክንያቶች ሌላ ሰው የፈጸመውን ወንጀል ተጠርጣሪው እራሱ እንደፈጸመው አድርጎ የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል።[15] ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የእምነት ቃል ለወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ጠቀሜታ እንዳለው ሁሉ በጥንቃቄ የማይመራ ከሆነ መርማሪ ፖሊሶች ተጠርጣሪው አምኗል በሚል ምክንያት ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዳያሰባስቡ በማዘናጋት ትክክለኛ ወንጀል የፈጸሙ ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር ባለመዋላቸው ማስረጃ ሊያጠፉና ከፍትህ ስርዓቱ ሊያመልጡ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል።[16] ስለሆነም መርማሪ ፖሊሶች በጥንቃቄ ሊሰሩት የሚገባው ጉዳይ የእምነት ቃል ከተጠርጣሪ በሚቀበሉበት ወቅት አንድም ተጠርጣሪው ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ እንዲሰጥ ማድረግ ሁለትም ማስረጃ በሚሰበስቡበት ወቅት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ በዝርዝር ማመኑን እንደ ስኬት በመቁጠር ቀጣይ ማስረጃዎችን ከማሰባሰብ መታቀብ ሳይሆን ከእምነት ቃሉ በመነሳት ሌሎች አሉ የሚባሉ ግዙፍነት ያላቸውንና ግዙፍነት የሌላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም መርማሪዎች ተጠርጣሪው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በዝርዝር አምኗል በማለት ሌሎች ማስረጃዎችን ከመሰብሰብ የሚቆጠቡ ከሆነ በክስ መመስረትና በክርክር ወቅት ዐቃቤ ህግ ወይም ፍርድ ቤት ማስረጃው ተዓማኒና አሳማኝ አይደለም

---

[12] ዝኒ ከማሁ
[13] ዝኒ ከማሁ
[14] ዝኒ ከማሁ
[15] ዝኒ ከማሁ
[16] ዝኒ ከማሁ

በማለት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያዙ ይችላሉ ወይም ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በውስጣዊና ውጫዊ ጫና ምክንያት በራሱ ነጻ ፍላጎት ስላልሆነ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት ክርክር በማንሳት ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።[17]

## 2. መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪ ቃል ሲቀበል ሊከተለው የሚገባ የቃል አቀባበል ስርዓት

በመርማሪ ፖሊስ የሚደረግ የተጠርጣሪ ቃል መቀበል ስራ ለወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራው ወሳኝ ምዕራፍ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። በእርግጥ የእምነት ቃል በወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ውስጥ አስተዋጽዖ የሚኖረው የተገኘው የእምነት ቃል ተጠርጣሪው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ከማናቸውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ የሰጠው የእምነት ቃል ሲሆን ነው። ከዚህም በላይ የእምነት ቃሉ የተገኘው ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊትና በሚሰጥበት ወቅት የተደረጉለት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards) በአግባቡ ተፈጻሚ ሆነው የተገኘ የእምነት ቃል ሲሆን ነው። በቃል መቀበል ወቅት የተጠርጣሪው ዝም የማለት ያለመናገር መብት እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ህንድና በሌሎች ሀገሮች ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥም ተካቶ የሚገኝ ነው።[18]

የተጠርጣሪ የቃል አቀባበል ስርዓትን አሁን ካለንበት ዘመን ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ሂደቶችንና ስርዓቶችን እንዳለፈ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ቀደም ባለው ጊዜ (በ1920ዎቹ እና 1930ዎቹ) አንድ ተጠርጣሪ የተጠረጠረበትን ወንጀል መፈጸሙን እንዲያምን ለማድረግ መርማሪ ፖሊሶች በስፋት የሚጠቀሙበት የቃል አቀባበል ስርዓት በማስገደድ ወይም ሀይል በመጠቀም (third degree method) በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የአካል እና የስነ-ልቦና ጉዳት በማድረስ የእምነት ቃል ለማግኘት የሚደረግ ጥረት እንደነበር የሚያመለክቱ ጽሁፎች አሉ።[19] ይህ ጊዜ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ አስቸጋሪ ዘመን የነበረበት ወቅት እንደነበር መገመት ይቻላል። ምክንያቱም በመደብደብ፣ በማሰቃየት፣ በማስገደድ፣ በማባበል /በመደለል/ በአጠቃላይ አላስፈላጊ የሆነ የአካልና የስነ-ልቦና ጉዳት በማድረስ የሚገኙ የእምነት ቃሎች በአንድ በኩል የእምነት ቃሉ በነጻ ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ የእምነት ቃልን መሰረት በማድረግ

---

[17] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967 ዓ.ም) አንቀጽ 134 እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(5) በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ውድቅ እንደሚሆን ያስቀምጣል።

[18] Zelman Cowen and P.B Carter, Essays on the evidence, (Oxford University, the claderon press, 1956), ገጽ 62

[19] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11

የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥ ንጹሀንንም ያለአግባብ ጥፋተኛ የሚያደርግበት አሰራር የሚኖርበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ በሌላ በኩል መንግስት ወንጀልን የማስረዳት ሀላፊነቱንና ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚያሳይ ሲሆን በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ ለመርማሪ ፖሊሶች ተግባሩ ማበረታቻ (bad incentive) በመሆን በቀጣይም በተመሳሳይ ስራ እንዲሳተፉ ከማድረጉም በላይ አንድ ሰው ራሱን ያለመወንጀል ህገ መንግስታዊ መብት ("the right not to incriminat one self") የሚጥስ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡[20] ይህ ተግባር በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና የህግ ምሁራን እንዲሁም በፍርድ ቤቶች ጭምር ትችት እየገጠመው እንደመጣ በዘርፉ የተጻፉ ጽሁፎች ያስገነዝባሉ፡፡[21] ይህንንም ተከትሎ በወንጀል ፍትህ ስርዓታቸው ከፍተኛ እድገት ያሳዩ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ውስጥ የእምነት ቃል በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት የተገኘ ለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት እየተዘረጋ መምጣት ጀመረ፡፡[22] ለምሳሌ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ1950ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ያስቀመጠው አሰራር ፍርድ ቤቶች የእምነት ቃልን እንደ ማስረጃ ከመውሰዳቸው በፊት ማስረጃው የተገኘው በፈቃደኝነት መሆን አለመሆኑን (voluntariness test) በሚባል አሰራር ፍርድ ቤቶች እንዲያጣሩ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋ እንዳደረገ በዚሁ ዙሪያ የተጻፉ ጽሁፎች ያመለክታሉ፡፡[23] ይህ ዘዴም በተጠርጣሪ የተሰጠ የእምነት ቃል ተጠርጣሪው ሳይገደድ በራሱ ነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፈቃዱ የሰጠው ነው አይደለም የሚለውን ለማጣራት ጥረት ይደረግ ስለነበር በተወሰነ መልኩም ቢሆን በተጠርጣሪዎች ላይ የሚደረገውን ጫና እንዲቀንስ ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል፡፡[24] ይህ አሰራር እየዳበረ መምጣቱ ተጠርጣሪውን ካላስፈላጊ መገደድ ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱ አስተዋጽዖ ነበረው ለማለት ይቻላል፡፡ የዚህ ስርዓት መዘርጋት ተጠርጣሪው ላይ የሚደርሰውን ስቃይና ጫና ከመቀነሱም በላይ በነጻ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ያልተሰጠ የእምነት ቃል ተዓማኒ ያልሆነ ነው በሚል ከማስረጃ ውድቅ መደረጉ ለተጠርጣው ከፍተኛ ድል ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በብዙ ሀገራት ሲሰራበት የነበረው የቃል አቀባበል ሂደት ዋና እና ማዕከላዊ ችግሩ በቃል መቀበል ወቅት መርማሪ ፖሊሶች የሚፈጽሙትን የማስገደድ ወይም የማባበል ተግባር እንዴት ሊቆም ይችላል? ተጠርጣሪው ጥያቄ ከመጠየቁ በፊት ምን ምን ስርዓት ሊሟላ ይገባል? ተጠርጣሪውን

---

20 ዝኒ ከማሁ

21 Jason K. Jensen, The Dilemma and Debate Over Confession and Evidence Strategies, ከ www.campbellcollaboration.org, ገጽ 13፣ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም ተወሰደ

22 ዝኒ ከማሁ

23 ዝኒ ከማሁ

24 ዝኒ ከማሁ

በመጠየቅ ሂደት ውስጥ ጥያቄዎቹ እንዴት መመራት አለባቸው? ቃሉ እንዴት ተቀባይነት ይኑረው? በሂደትም የእምነት ቃሉ ተቀባይነት እንዲኖረው የእምነት ቃሉ በፈቃደኝነት፣ በፍትሀዊነት፣ በነጻ ፍላጎት እና በህግ አግባብ የተሰጠ ከሆነ ነው የሚሉት ነጥቦች እየዳበሩ እንዲመጡና የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ሂደት አሁን ለደረሰበት ደረጃ መድረስ የራሱን አሻራ ጥሎ ያለፈ በመሆኑ ነው።[25] አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃሉን የሰጠው በነጻነትና በራሱ ፍላጎት ላይ በመመስረት እንዲሆን ለማስቻል የሚረዱ ስርዓቶች (The due process test) ዘዴዎች እንዲዘረጉ ተደርጓል።[26] ይህ ስርዓትም የእምነት ቃል አሰጣጥን በተመለከተ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እንዲመጣና አዳዲስ ስርዓቶችና በይበልጥ የተጠርጣሪውን መብት ሊያስጠብቁ የሚችሉ ስርዓቶች እንዲመጡ በማድረግ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አበርክቷል።

የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ አሁን ስራ ላይ ያለው የቃል አቀባበል ስርዓት ምን ምን ሁኔታዎችን ማሟላት እንደሚገባው የሚያሳዩ መሰረታዊ መርሆዎች በብዙ ሀገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግጋትና የወንጀል ፍትህ ፖሊሲዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።[27] አሁን በብዙ አገራት ላይ ለተዘረጋው የተጠርጣሪ የቃል አቀባበል ስርዓት እንደ ትልቅ መነሻ ተደርጎ የሚወሰደውና በብዙ ሀገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግጋት ውስጥ ተካቶ የሚገኘው በ1960 ዎቹ በአሜሪካን ሀገር ሚራንዳ በተባለ ግለሰብና በአሪዞና ግዛት መካከል የነበረውን የወንጀል ክርክር መነሻ በማድረግ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ ነው። ይህ ውሳኔ በተለይ አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት፡-

*"ሀ. ያለመገደድ መብት ያለው ስለመሆኑ፤*

*ለ. ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው ስለመሆኑ፤*

*ሐ. የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በፍርድ ቤት እንደማስረጃ እንደሚቀርብበት ሊነገረው እንደሚገባ እና*

*መ. ጠበቃ የማማከር መብት ያለው መሆኑ ሊነገረው እንደሚገባ በግልጽ አስቀምጧል:[28]"*

[25] John Sankey, Basic rules of law enforcement on Miranda warning and anti-torture warning www.campbellcollaboration.org, ገጽ 23፣ ሚያዚያ 24/2011 ዓ.ም ተወሰደ

[26] ዝኒ ከማሁ

[27] የኢትዮጵያ፣ የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የህንድና የሌሎች አገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎች ውስጥ ተካቶ ይገኛል።

[28] ዝኒ ከማሁ

በዚህ ውሳኔ መሰረት አንድ ተጠርጣሪ ለመርማሪ ፖሊስ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ከመደረጉ በፊት በፖሊስ ሊገለጽለት የሚገቡ መብቶች ተብለው የተቀመጡ ሲሆን እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችም ተጠርጣሪው ለፖሊስ ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት አላግባብ በተጽዕኖ ስር እንዳይወድቅ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards) ናቸው፡፡ እነዚህ መርሆዎችም በተለምዶ የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች (Miranda warnings) ተብለው ይታወቃሉ፡፡[29] ይህ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል ምን መስፈርትን መከተል አለበት በሚለው ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ እንደነበርና ከውሳኔው በኋላ ብዙ አገራት በወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎቻቸው ውስጥ አካተውት እንደሚገኝ ይገለጻል፡፡[30] እነዚህን ለተጠርጣሪው የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (መብቶችን) መርማሪ ፖሊስ ለተጠርጣሪው መግለጹ ብቻ በቂ አይደለም ይልቁንም ተጠርጣሪው መብቶቹን በአግባቡ መረዳቱን ማስገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡[31] ስለሆነም ፍርድ ቤቶች አንድን የተጠርጣሪ የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ ከመቀበላቸው በፊት የእምነት ቃሉ የተገኘው የሚራንዳ መርሆዎች (miranda warnings) ተሟልተውና የተጠርጣሪው መብት በፖሊስ የተነገረው መሆኑን ፖሊስ እንዲያረጋግጥ በማድረግ መሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡[32] በተጨማሪም ፖሊስ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በህግ የተቀመጡትን መብቶቹን ለማለፍ በሙሉ ግንዛቤና እውቀት (knowingly and intelligently) እንደሆነ እንዲሁም በፈቃደኝነት (voluntarily) መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡[33]

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እነዚህን የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች ሲወስን መነሻ ያደረገው በአሜሪካ ህገ መንግስት እንዲሁም ሰብዓዊ መብትን ለመደንገግ በተለያዩ የዓለም ዓቀፍ ሰነዶች ላይ የተቀመጡ የተጠርጣሪ መብቶችን የሚደነግጉ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡[34] ለዚህ ውሳኔ መነሻ ከሆኑ የተጠርጣሪ መብቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ማንኛውም ተጠርጣሪ እራሱን ያለመወንጀል መብት (privilege against self-incrimination) መብት ያለው መሆኑን የሚደነግገው የተጠርጣሪዎች ህገ መንግስታዊና በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ሰነዶች ላይ የተደነገገው መብት ነው፡፡[35] ይህ መብት የሚያረጋግጠው ማንኛውም ተጠርጣሪ እራሱን ያለመወንጀል መብት ያለው መሆኑን ሲሆን በሌላ በኩል ወንጀልን የማስረዳት ሀላፊነት በመንግስት ጫንቃ ላይ ያረፈ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ መብት

[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 30
[30] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 26
[31] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24
[32] ዝኒ ከማሁ ገጽ 31
[33] ዝኒ ከማሁ ገጽ 35
[34] ዝኒ ከማሁ
[35] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12

ተፈጻሚ መሆን የሚገባው በፖሊስ ከቅድመ ቃል መቀበል ጀምሮ እስከ ፍርድ ሂደቱ መጨረሻ ድረስ ነው በሚል እምነት ነው፡፡ አንድ ተጠርጣሪ ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ ራሱን ሊያስወነጅል የሚችል ነገር ካለ ዝም በማለት ራሱን የሚያስወነጅለውን ጉዳይ ከመግለጽ ሊቆጠብ ይችላል፡፡ በእርግጥ ይህ ማንኛውም ሰው ራስን ያለመወንጀል መብት ያለው መብት የሚመነጨው እንደ ንጹህ ሆኖ ከመቆጠር መብት ነው፡፡[36] ምክንያቱም ራስን ያለመወንጀል መብት የሚከበረው በዋናነት ማንኛውም ሰው ከፍርድ በፊት እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው ከሚለው በመነሳት ነው፡፡[37] ይህ ማለት ራስን ያለመወንጀል መብት ሊረጋገጥ የሚችለው ዝም የማለት መብት ሲረጋገጥ ነው ከሚል አመክንዮት በመነሳት ነው፡፡ በዚህም መሰረት እራስን ያለመወንጀል መብት ሲረጋገጥ ማንኛውም ተጠርጣሪ /ተከሳሽ/ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብትን ያረጋግጣል በሚል ይገለጻል፡፡[38] በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ በግልጽ ራስን ያለመወንጀል መብት የተደነገገው ለምስክሮች ሲሆን እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት ግን ለተከሳሽ የተሰጠ መብት ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት **ዝም የማለት መብት ለተከሳሹ** የሚያገለግል ሲሆን **ራስን ያለመወንጀል መብት ግን ለምስክሮችም** ያገለግላል በማለት ያስቀምጣሉ፡፡[39] ሁለቱም የሚመነጩት ለተጠርጣሪና ለምስክሮች ከሚደረግ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ሌላው የሚራንዳ መርሆዎችን ለመወሰን መነሻ የሆነው አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ሲሰጥ ቃሉ የተገኘበትን መንገድ የሚያረጋግጠው ስርዓት የተገኘበት ሂደት በፈቃደኝነት ነውን በሚል የሚለካበት ሂደት (The due process voluntariness test) ነው፡፡[40] ከዚህም ሌላ የወንጀል ጉዳዮችን የማስረዳት ሀላፊነት የመንግስት እንደ መሆኑ መጠን ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ከየትኛውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ቃል የተቀበለው መርማሪ ነው ከሚል መርህ በመነሳት ነው፡፡ ከላይ ከተቀመጡት ምክንያቶች በተጨማሪ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት የሆነው ሌላው ጉዳይ ማንኛውም ተጠርጣሪ ጠበቃ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግገው የህገ መንግስቱ ድንጋጌ ነው፡፡[41] አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ የማማከር መብት

---

[36] ዝኒ ከማሁ ገጽ 134

[37] ዝኒ ከማሁ

[38] ዝኒ ከማሁ

[39] Aderajew Teklu and Kedir Mohammed, teaching materials (unpublished), March, 2009, Addis Ababa ገጽ 5

[40] ዝኒ ከማሁ ገጽ 138

[41] RICHARD A. LEO" AND RICHARD J., THE CONSEQUENCES OF FALSE CONFESSIONS: DEPRIVATIONS OF LIBERTY AND MISCARRIAGES OF JUSTICE IN THE AGE OF PSYCHOLOGICAL INTERROGATION, ገጽ 145፣ ከ www.wcjsc.org/ ድህረ ገጽ የተወሰደ ሚያዚያ 26/2011 ዓ.ም

መከበር ያለበት ከቃል መቀበል ወቅት ጀምሮ መሆን ይገባዋል ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት ነው፡፡[42] ምክንያቱም የጠበቃው መኖር መርማሪ ፖሊስ የሚያደርሳቸው ተጽዕኖዎች አይኖሩም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ተጠርጣሪው ከላይ የተቀመጡትን መብቶቹን በግልጽ ካልተዋቸው በስተቀር ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ሊፈጸምለት ይገባል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሚራንዳ በተባለ ግለሰብና በአሪዞና ግዛት መካከል የተደረገው ክርክርና የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በተለይ መንግስት በአንድ በኩል ወንጀልን የመቆጣጠር ሀላፊነት ያለው መሆኑንና በሌላ በኩል አንድ ተጠርጣሪ እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብቱ እንዳይሸረሸር፣ ያለመገደድ መብት ያለው መሆኑን፣ ለተጠርጣሪው በህግ የተደረገለትን ጥበቃ የሚያሳይና ፖሊስ የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል በፍርድ ቤትና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የማድረግ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ያረጋገጠ እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ አሁን በብዙ ሀገራት የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የእምነት ቃል አወሳሰድ ስርዓትም አንድ ተጠርጣሪ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ አንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለው በማድረግ ፍርድ ቤቱ የቃል አቀባበል ስርዓት የተሰጠው የእምነት ቃል ፍትሀዊ እና በነጻ ፍላጎት የተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እነዚህን ጥበቃዎች ለማድረግ ጥረት የሚደረግበት ምክንያት ተጠርጣሪው ተገዶ የእምነት ቃል እንዳይሰጥ ለመከላከል ነው፡፡. ስለሆነም ፍርድ ቤቱ የተገኘውን የእምነት ቃል ከማስረጃ ምዘና ውስጥ እንዲያስገባው ከተፈለገ የእምነት ቃሉ የተሰጠው በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት፣ ያለምንም ተጽዕኖና ለተጠርጣሪው የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችን መሰረት አድርጎ የተገኘ መሆን እንደሚገባው ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 3. የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት

መነሻቸውን ከአውሮፓ ያደረጉት "የሲቭልና የኮመን" ሎው የህግ ስርዓቶች ለኢትዮጵያ የዘመናዊ የህግ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳበረከቱ ይታመናል፡፡[43] ኢትዮጵያ በዋናነት ዘመናዊ ህጎቿን ስትቀርጽ እነዚህን ሁለት የህግ ስርዓቶች በተለይም "የሲቭል ሎው" የህግ ስርዓትን እንደ ዋነኛ ምንጭ በመውሰድ የተለያዩ ህጎችን በማጽደቅ ሀገሪቱ የዳበረ የህግ ስርዓት እንዲኖራት በማድረግ ረገድ ትልቅ እርምጃ እንደተወሰደ ይታመናል፡፡[44] ከምዕራባውያን የህግ ስርዓት ("ከሲቪልና ኮመን ሎው") የህግ ስርዓቶች ተቀድተው ስራ ላይ

---

[42] የግርጌ ማስታወሻ 30

[43] "የሲቪልና የኮመን ሎው" የህግ ስርዓቶች በብዙ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ ለህግ ስርዓት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑ በተለያዩ ጽሁፎች የሚያመለክቱ ጽሁፎች የተገለጸ ሲሆን ከዚህም አልፎ ብዙ የሀገራችን ህግ መምህራን ይህን ሲገልጹ ይሰማል፡፡

[44] Stanely Z. Fisher, Ethiopian criminal procedure, A source Book, (Adiss Ababa, Faculty of law, HSIU, 1966), ገጽ 8

ከዋሉት ህጎቻችን ውስጥ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ተጠቃሽ ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ውስጥ ምርመራ እንዴት ይከናወናል፤ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች እንዴት በቁጥጥር ስር ሊውሉ ይችላሉ፤ የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት ምን መርህ መከተል አለበት፤ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳይ ክርክር በፍርድ ቤት እንዴት እንደሚመራና ሌሎችንም ዝርዝር ድንጋጌዎችን በመያዝ በወንጀል ጉዳዮች ላይ በአንድ በኩል አጥፊዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚችሉበትን ስርዓት ለመዘርጋት በሌላ በኩል ተጠርጣሪዎች በምርመራ ጊዜና በክርክር ወቅት አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገቡ ሊከላከሉ የሚችሉ ስርዓቶችንና የተጠርጣሪ መብቶችን የያዙ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተካተውበት ይገኛል፡፡[45] እነዚህ የተጠርጣሪና የተከሳሽ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዋናነት ዓላማ አድርገው የተቀረጹት በወንጀል መከላከልና ወንጀለኞችን ለፍትህ ለማቅረብ በሚደረገው ሂደት ውስጥ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ በመንግስት (በህግ አስፈጻሚው) ስልጣን ላይ ገደብ በማስቀመጥ በወንጀል ምርመራና ክስ ሂደት ያለውን ስራ ሚዛናዊ አድርጎ ለማስኬድ በማሰብ ነው፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ ውስጥ አንድ ተጠርጣሪ መቼና እንዴት በቁጥጥር ስር ሊውል ይገባል፣ ተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉና በምን ሁኔታ እንደሚሰጥ፣ ምርመራው እንዴት እንደሚከናወንና ከምርመራ በኋላም ክርክሩ እንዴት እንደሚመራ የሚያመለክቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡[46]

በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ተጠርጣሪ ወንጀል ለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ የሚፈጥር ምክንያት (reasonable suspition) በተገኘ ጊዜ ፖሊስ ምርመራ ለማከናወን እንዲያስችለው ተጠርጣሪው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 25 መሰረት እንዲቀርብ መጥሪያ ሊልክለት ይችላል ወይም በዚሁ ስነ-ስርዓት ህግ በአንቀጽ 26፣ 50 እና 51 መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ሊያውለው ይችላል፡፡ በወንጀል ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር የዋለ ተጠርጣሪ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ተጠርጣሪው ስሙን፣ አድራሻውንና ግላዊ ሁኔታውን የሚገልጹ ጉዳዮቹን ሊገልጽ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡[47] ተጠርጣሪው ስሙንና አድራሻውን ከገለጸ በኋላ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የቃል አቀባበል ስርዓቱ የተለያዩ መርሆዎችን መከተል እንዳለበት በዚሁ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ተደንግጎ

[45] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967)፣ አንቀጽ 25፣ 27(2)፣ 29፣ 35፣ 46፣ 54 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡
[46] ዝኒ ከማሁ
[47] የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 27(1)

ይገኛል።[48] እነዚህ የእምነት ቃል አቀባበል ስርዓቶች ከወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር ተደንግገዋል። ይህም የሚያሳየው የተጠርጣሪ ቃል አቀባበልን የሚመለከቱ ስርዓቶችና የተጠርጣሪ መብቶች በህገ መንግስት ጭምር ዋስትና ያገኙ መብቶች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 27(2) ስር በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃል ተቀባዩ ፖሊስ ለተጠርጣሪው ሊገልጽለት ይገባል ተብለው የተቀመጡት የተጠርጣሪው መብቶችና መርሆዎች በሚከተለው መልኩ ተገልጸው ይገኛሉ።

***ሀ. "ተጠርጣሪው ምላሽ እንዲሰጥ ለማስገደድ አይቻልም፤ ነገር ግን ምላሽ ለመስጠት ነጻ እንደሆነና ፈቅዶ የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑን ጠያቂው ፖሊስ ለተጠርጣሪው መንገር ይገባዋል"።***

***ለ. "ማንኛውም የተሰጠ ቃል መመዝገብ አለበት"።***

ከላይ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ የተመለከቱት በቃል መስጠት ጊዜ ሊከበሩ የሚገቡ የተጠርጣሪ መብቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር እንደሚከተለው ተቀምጠዋል። ***"የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፤ የሚሰጡት ማናቸውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ሊነገራቸው ይገባል"*** በሚል ተቀምጦ ይገኛል።

እነዚህ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በግልጽ የተመለከቱት የተጠርጣሪ መብቶች የተቀመጡበት ምክንያት ምንድን ነው ብለን ብንጠይቅ በወንጀል ምርመራ ወቅት የመንግስትና የተጠርጣሪዎች አቅም በእጅጉ የተራራቀ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገቡ የቃል አቀባበል ስርዓት በመዘርጋት ለተጠርጣሪዎች ጥበቃ ለማድረግ በማሰብ የተደነገጉ ናቸው። በወንጀል ጉዳዮች ላይ ተጠርጣሪው ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ የማስረዳት ተፈጥሯዊ ሀላፊነት /inherent responciblity/ ያለበት መንግስት ሲሆን የሚሰበስቡት ማስረጃዎችም ተቀባይነትና አግባብነት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። ምክንያቱም የወንጀል ምርመራ ስራ የሚደረገው ሁለት ፈጽሞ የማይነጻጸር ጉልበት ባላቸው አካላት መካከል ነው። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት መብቶች የተደነገጉበት ዋናው ምክንያት መርማሪ ፖሊስ ወይም ስልጣን የተሰጠው አካል ተጠርጣሪውን በመደለል፣ በማባበል፣ የተስፋ ቃል በመስጠት፣ በማስፈራራት፣ የሀይል ስራ ወይም ሌሎች ከህግ ውጭ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም

---

48 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 27(2)

ከተጠርጣሪው የእምነት ቃል ለማግኘት በሚደረግ ጥረት ውስጥ የተጠርጣሪው ሰብዓዊና መሰረታዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለማድረግ የተቀመጡ መርሆዎች ናቸው፡፡ ተጠርጣሪው ከተጠረጠረበት ወንጀል ጋር በተያያዘ ምንም ነገር ለመናገር ካልፈለገ ዝም ማለት እንዲችል መብት የተሰጠውም ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከተጠርጣሪው ፍላጎት ውጭ የእምነት ቃል እንዳይገኝ ለማድረግ ነው፡፡ ቃል ተቀባዩ ፖሊስም ቃል ከመቀበሉ በፊት ተጠርጣሪው ዝም የማለት መብት ያለው መሆኑን እንዲገልጽ በህጉ ላይ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ይህ ሲሆን ተጠርጣሪው ምን ምን መብት እንዳለው ይገነዘባል እንዲሁም የሚሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት የሚሰጠው ዋጋ (credibility /weghit/) ከፍ ይላል፡፡ አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ያሉት መብቶች ሲነገሩት በምርመራ ወቅት ዝም ማለቱ ወንጀሉን እንዳመነ ተደርጎ እንዳይወሰድበት ያለውን ስጋት ይቀንሳል፤ ተጠርጣሪው ዝም በማለቱ በፍርድ ቤቶች ዘንድ ወንጀሉን እንዳመነ ተደርጎ እንደማይቆጠርበትም ይረዳል፡፡ መብቶቹ እንዲነገሩት የሚደረግበት ዋናው ምክንያትም እነዚህ መብቶች ለተጠርጣሪው ሲነገሩት ተጠርጣሪው እስቦ የሚጠቅመውን በመምረጥ መናገር አለብኝ ወይስ የለብኝም የሚለውን በማሰብ የሚጠቅመውን ለመወሰን እንዲችል ለማድረግ ነው፡፡[49] በተጨማሪም ተጠርጣሪው የሚናገረው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ብቻ እንደሆነ እንዲረዳ ለማስቻል ነው፡፡ ሆኖም ተጠርጣሪው መብቶቹ በመርማሪው ፖሊስ ከተገለጹለት በኋላ መብቶቹን ላይጠቀምባቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ዝም የማለት ያለመናገር መብቱን አልፎ ቃሉን ሊሰጥ ይችላል ወይም አለመናገርን ሊመርጥ ይችላል፡፡ የሚናገር ከሆነም የተናገረው ነገር ሁሉ እንደ ማስረጃ ሆኖ እንደሚቀርብበት በሙሉ ግንዛቤ አውቆ ይወስናል፤ መናገሩ የሚያስከትለውን ውጤትም ይቀበላል ማለት ነው፡፡

አንድ ተጠርጣሪ ዝም የማለት መብቱን በመተው በምርመራ ወቅትም ሆነ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ እያለ ዝም የማለት መብቱን በመተው የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ዝም የማለት መብቱን በማለፍ ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ቃሉ ሳይቀነስና ሳይጨመር ተጽፎ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ የተናገረው ቃል እንዲነበብለት እና አንብቦ እንዲፈርም መደረግ እንዳለበትም በህጉ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ክርክሩ በሚታይበት ወቅት በፍርድ ቤትም ተጠርጣሪው መናገር ከፈለገ ቃሉን ከውሳኔ በፊት በማንኛውም ጊዜ ስለወንጀል አፈጻጸሙ በማመን በዝርዝር ለመናገር መብት አለው፡፡

[49] Christian A. Meissner, Allison D. Redlich, interview and interrogation methods and their effects on true and false confessions, ገጽ 87 በ www.http://ilab.utep.edu ላይ ይገኛል ሚያዚያ 23/20011 ዓ.ም የተወሰደ

አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ዝም የማለት መብት ከመጎናጸፉም በላይ እንደ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ህንድና ሌሎች አገራት በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት **አንድ ተጠርጣሪ** በቅድመ ክስ ሂደት ወቅት ጠበቃ እንዲያገኝ የሚያስችል የህግ ስርዓት አላቸው፡፡[50] በእንግሊዝ የህግ ስርዓት ዝም የማለት መብቱን በማለፍ በጠበቃው ፊት የሚሰጠው ቃል ያለተጨማሪ ማስረጃ ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን በመቀበል ከማስረጃ ምዘና ውስጥ በማካተት ውሳኔ እንደሚሰጡበት ጽሁፎች ያሳያሉ፡፡[51] ምክንያቱም ጠበቃው በሚሰጠው ምክር መሰረት ያለመናገር መብቱን በመተው በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት ቃሉን እንደሰጠ ከመገመቱም በላይ ከማናቸውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ ቃሉን እንደሰጠ ስለሚታመን ነው፡፡ ምክንያቱም ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ጠበቃው ፊት ለፊቱ ስለሆነ የትኛውም ዓይነት ጫናና ማስገደድ ይኖራል ተብሎ ስለማይታመን ነው፡፡ በሌላ በኩል በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት አንድ ተጠርጣሪ የእምት ክህደት ቃሉን የሚሰጠው የቅድመ ክስ የወንጀል ጉዳዮችን ማለትም የዋስትና፣ የጊዜ ቀጠሮና የምርመራ ጉዳዮችን ለማከናወን ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ፊት በመሆኑና ይህ ፍርድ ቤትም ገለልተኛ አካል በመሆኑ በዚህ አግባብ የተሰጠ የእምነት ቃል ጉዳዩን በሚያየው ፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ይወሰዳል፡፡[52]

ከላይ እንደተመለከትነው በሌሎች አገሮች ጠበቃ የማማከር መብት በቃል መቀበል ወቅት /at the time of interrogation/ እንደሚጀምር ተመልክተናል፡፡ በተመሳሳይ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ጠበቃ የማማከር መብት በምርመራ ወቅት እንደሚጀምር የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ውስጥ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 61 ስር ለምርመራ በማረፊያ ቤት የሚገኝ ተጠርጣሪ ጠበቃውን የማማከር መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 21(2) ስር ማንኛውም ተጠርጣሪ በጠበቃውና በቤተሰቡ የመጎብኘት መብት እንዳለው ተቀምጧል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ ላይ እንደተገለጸው አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ የማግኘት መብቱ የሚጀምረው በቃል መቀበል ወቅት ወይም ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለበት ቅጽበት ጀምሮ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት የህግ ክፍሎች ውስጥ ጠበቃ የማማከር መብት የሚጀምረው አንድ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ቅጽበት ጀምሮ በምርመራ ወቅት ጭምር እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ ይሁን

[50] ዝኒ ከማሁ
[51] ዝኒ ከማሁ
[52] ዝኒ ከማሁ

እንጂ በምርመራ ወቅት ጠበቃ ከማማከር ጋር በተገናኘ በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ በቃል መቀበልና የምርመራ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ጠበቃው የቃል መቀበሉ ስራ በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ ሂደቱን እንዲከታተል የሚፈቅድ አሰራር የለም፡፡[53] በእርግጥ ከላይ የተመለከትናቸው ድንጋጌዎች የአንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ሂደቱን ልከታተል በማለት አቤቱታ ቢያቀርብ ህጉ የሚከለክል አይደለም፡፡ በተግባር በስፋት ያለው አሰራር የሚያመለክተው ግን የቃል መቀበል ስራ የሚከናወነው ጠበቃ ባለበት ይቅርና ሌሎች ሰዎች በሌሉበት በጠባብ ክፍል ውስጥ ነው፡፡[54] ይህም በመሆኑ ምክንያት ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ የሰጠነው የእምነት ቃል በሀይልና በተጽዕኖ እንዲሁም መብታችን ሳይነገረን ስለሆነ ማስረጃው ሊያዝብን አይገባም የሚል አቤቱታ በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ ይታያል፡፡[55] ይህንን ተቃውሞ ለመከላከል በሚል እምነት መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪውን ቃል በሚቀበልበት ወቅት ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎትና ሳይገደድ መሆኑን ለማስረዳት የደረጃ ምስክር ባለበት የቃል መቀበል ሂደት እንደሚከናወን ይገለጻል፡፡[56] በእርግጥ የደረጃ ምስክር በመሆን የቃል መቀበል ሂደቱን የሚከታተሉት ብዙ ጊዜ የምርመራ ስራ በሚከናወንበት ፖሊስ ጣቢያ የሚሰሩ የፖሊስ ባልደረቦች ናቸው፡፡[57] ሌላው ጠበቃ ከማግኘት መብት ጋር በተገናኘ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ከክስ በፊት በምርመራ ወቅት ጠበቃ ለማማከር የሚችሉት በግል ጠበቃ የመቅጠር አቅም ያላቸው ተጠርጣሪዎች ብቻ እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 20(5) ስር እንደተገለጸው አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ በራሱ ማቆም ካልቻለ በመንግስት ወጭ ጠበቃ ሊቆምለት የሚችለው ክስ ከቀረበበት በኋላ ጉዳዩ በክርክር ላይ ባለበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ለተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በምርመራ ወቅት በመንግስት ወጭ ተከላካይ ጠበቃ የማግኘት መብት የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ክስ ከቀረበ በኋላ በክርክር ወቅትም ቢሆን በመንግስት ወጭ ጠበቃ እንዲቆም የሚደረገው እንደ ሰው መግደል፣ ከባድ ውንብድናና ሌሎች ከባድ ወንጀሎች በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ባለመቆሙ ምክንያት ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም ሲወስን የሚፈጸም ስለሆነ ወጥ የሆነ አሰራር

---

[53] የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በተለያዩ ወቅቶች በተለይም በ2007 ዓ.ም በአማራ ክልል በሁሉም ዞኖች ለሚገኙ መርማሪ ፖሊሶች ስልጠና በሰጠሁበት ወቅት የቃል መቀበል ስራ በሚከናወንበት ወቅት ጠበቃም ሆነ ሌሎች ሰዎች በሌሉበት እንደሚከናወን ከመርማሪዎቹ ጋር ከተደረገ ውይይት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

[54] ዝኒ ከማሁ

[55] ዝኒ ከማሁ

[56] ዝኒ ከማሁ፣ እንዲሁም የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በስራ አጋጣሚ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን በራሱ ፍላጎት የሰተ ለመሆኑ ያረጋግጣሉ በሚል የደረጃ ምስክር የቀረቡባቸውን የተለያዩ መዝገቦች ለማየት ችያለሁ፡፡

[57] ዝኒ ከማሁ

የለም፡፡[58] ስለሆነም በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት አንድ ተጠርጣሪ በጠበቃው ፊት ቃሉን የሚሰጥበት ወቅት ካለመኖሩም በላይ በመንግስት ወጭ ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም የሚደረገው ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ባለበት ወቅት ለከባድ ወንጀሎችና ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ ካልቆመ ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ነው፡፡

## 3.1 ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት አሰራር

አንድ ተጠርጣሪ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ቃሉን በቃል መቀበል ወቅት ለመርማሪ ፖሊስ ሊሰጥ ይችላል ወይም ጉዳዩ በክርክር ላይ ባለበት ወቅት ለፍርድ ቤት የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ማለት የእምነት ቃል ከፍርድ ቤት ውጭ ወይም በፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ሁለቱም ዓይነት የእምነት ቃል አሰጣጦች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ለፖሊስ የሚሰጠው ቃል በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ. በአንቀጽ 27(1 እና 2) ስር የተመለከተ ሲሆን ለፍርድ ቤት የሚሰጥ የእምነት ቃል ደግሞ በዚሁ ህግ በአንቀጽ 35፣ 85 እና 134 መሰረት የሚሰጥበት ሁኔታ ነው፡፡ በዚሁ ህግ በአንቀጽ 85 መሰረት የሚሰጠው ቃል ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ በሚታይበት ጊዜ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተከሳሹ የሚሰጠው ቃል ካለና ቃሉን ለመስጠት በራሱ ነጻ ፍላጎት ከወሰነ ቃሉን ይሰጥና ተመዝግቦ ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት ይላካል፡፡ በሌላ በኩል በአንቀጽ 134 ስር የሚሰጠው የእምነት ቃል ተከሳሹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ወንጀል ስለመፈጸሙና ጥፋተኛ መሆኑንም በማረጋገጥ ስለድርጊት አፈጻጸሙ በዝርዝር ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት የሚያስረዳበት ስርዓት ነው፡፡ በዚሁ የእምነት ቃል መሰረትም ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል ህጉ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ የእምነት ቃሉን መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ካለው የእምነት ቃሉን በማለፍ ሌሎች ማስረጃዎች እንዲሰሙ /እንዲቀርቡ/ ሊያደርግ የሚችልበት ስልጣንም ተሰጥቶታል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ መሰረት ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ ከሚደረግበት አግባብ አንዱ በዚሁ ስነ-ስርዓት ህግ በአንቀጽ 35 ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ከተሰጠ ራሱን ችሎ እንደ ማስረጃ የሚወሰድና ተቀባይነት አግኝቶ ከማስረጃ ምዘና ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ 35 በተገለጸው መሰረት ተጠርጣሪ ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎት

[58] በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት በደብረ ብርሀን ቋሚ ምድብ ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህግ ጋር ግንቦት 11/2011 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ

ለመስጠት የወሰነ እንደሆነ ተጠርጣሪው የሚሰጠውን ቃል ፍርድ ቤቱ ለመቀበል እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ተጠርጣሪው የሚሰጠው ማናቸውም ቃል ሳይጓደል በመመዝገብ የተሰጠውን የእምነት ቃልም ለዐቃቤ ህግ እና ዋናውን ጉዳይ የሚመለከተው ሌላ ፍርድ ቤት በሆነ ጊዜ ይሄው ማስረጃ ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት እንደሚላክ ተደንግጓል፡፡[59] በተግባር ያለውን አሰራርም ስንመለከት መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪውን ቃል ከተቀበለ በኂላ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ አምኗል የሚል ግምት ሲኖረው በግዛት ስልጣኑ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት በመውሰድ የተሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረብ ፍርድ ቤቶችም በስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 35 በተቀመጠው አግባብ የእምነት ቃል ሲያረጋግጡ ይስተዋላል፡፡ የቃል አቀባበል ስርዓቱ የሚፈጸመውም በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ 35 መሰረት በተገለጸው መንገድ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቀደም ሲል ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ መደረግ ያለበት ስርዓት ተጠብቆና የስነ-ስርዓት ህጉ ጥበቃዎች (የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች) ተነግረውት መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ታዲያ ከዚህ ስነ-ስርዓታዊ ድንጋጌና በተግባር ከሚሰራው ጋር በተያዘ የሚነሳው ጥያቄ በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 27(2) መሰረት ስነ-ስርዓት ህጉ በሚያዘው አግባብ የተሰጠ የእምነት ቃል ተቀባይነት ያለውና ከማስረጃ ምዝና ውስጥ የሚገባ ከሆነ በዚሁ ህግ በስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 35 የተቀመጠው ድንጋጌ አላማው ምንድን ነው? ከስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 27(2) ጋር ሲታይ ድግግሞሽ አይሆንምን? የሚል ሀሳብ በባለሙያዎች ዘንድ ሲነሳ ይታያል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 35 ስር የተቀመጠውን በሚመለከት ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦች በባለሙዎች ዘንድ ሲነሱ ይታያል፡፡ የመጀመሪያውን ክርክር የሚያቀርቡ ባለሙያዎች እንደሚሉት በስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 27(2) እና በአንቀጽ 35 ስር ያሉት ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለው የቆሙ ሳይሆን ተደጋጋፊ ናቸው፡፡[60] ምክንያቱም በአንቀጽ 27(2) መሰረት ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት ዋናው ምክንያት ዳኞች ከክርክሩ የመጨረሻ ውጤት (out come of the case) የሚያገኙት ምንም ጥቅም ስለሌለ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የተጠርጣሪውን ቃል መቀበል ስለሚችሉ ህግ አውጭው ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ ሲደረግ ተዓማኒ መሆኑን በማሰብ የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ሲሉ ያስቀምጣሉ፡፡[61] በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ችሎት የሚያስችሉት በግልጽ ችሎት በመሆኑ ምናልባትም የትኛውም ሰው ሊመለከት በሚችል ደረጃ ስለሆነ ተጠርጣሪው

---

[59] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 35
[60] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58
[61] ዝኒ ከማሁ

በነጻነትና በሙሉ ፍላጎት ቃሉን ለመስጠት የሚችልበት እድል አለው በሚል ነው፡፡[62] በሌላ በኩል ፖሊስ ቃል የሚቀበለው ምናልባትም ሰው በማይኖርበት ቦታ፣ በጠባብ ክፍል ውስጥ፣ የቦታው ሁኔታ በራሱ ፍርሀትና ጭንቀት የሚፈጥር፣ መርማሪ ፖሊሱ የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎትና ጥረት የሚያደርግበት ሁኔታ ስላለ በየትኛውም ሁኔታ ተጠርጣሪው ነጻ ሆኖ ሊሰጥ የሚችልበት እድል ስለሌለ በወ.መ.ስ.ስ.ህ አንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የሚሰጥ ቃል ብቻውን ተዓማኒ ሊሆን አይችልም የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡[63] በሌላ በኩል ከላይ የተቀመጠውን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወ.መ.ስ.ስ.ህ. በአንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ራሱን ችሎ የቆመና በራሱ እንደ ማስረጃ እንደሚወሰድ ህጉ በግልጽ ያስቀመጠው ስለሆነ በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት አሰራር በልምድ የመጣ እንጂ የስነ-ስርዓት ህጉን ዓላማ የተከተለ አይደለም የሚል ክርክር ያነሳሉ፡፡[64] እነዚህ ባለሙያዎች ጨምረው የሚያነሱት ጉዳይ ምናልባት ተጠርጣሪው በ27(2) መሰረት ካመነ በኋላ በፍርድ ቤት ወንጀሉን መፈጸሙን ቢክድ ለፖሊስ የሰጠውን የእምነት ቃል ውድቅ ለማድረግ ወይም ማስረጃው ተዓማኒ አይደለም በማለት ማስረጃውን ውድቅ ለማድረግ ወይም ክብደቱን ዝቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም የሚል ክርክር ያነሳሉ፡፡[65] እነዚሁ ባለሙያዎች እንደሚሉት ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት መረጋገጥ አለበት የሚል ክርክር የሚያነሱ ባለሙያዎች ዓላማቸው ለፖሊስ የተሰጠው ቃል በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥ የእምነት ቃሉ ተዓማኒ ሊሆን አይችልም የሚል ከሆነ ተጠርጠሪው ቃሉን በፍርድ ቤት ከሰጠ በኋላ ተመልሶ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚሄድ ቀድሞ ከተናገረው ቃል ውጭ ቢናገር ሊገጥመው የሚችለውን የሀይልም ሆነ የስነ-ልበና ጉዳት እያሰበ አልፎ አልፎም ቃልህን የምትቀይር ከሆነ በሚል በመርማሪ ፖሊስ ዛቻ እየተዛተበት ወደ ፍርድ ቤት ስለሚሄድ ለፖሊስ ከሰጠው ቃል የተለየ ነገር ይናገራል ተብሎ አይጠበቀም የሚል ክርክር ያቀርባሉ፡፡[66] ይህንን ነጥብ በሚመለከት የጸሀፊው እምነት በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 35 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ዓላማ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል በነጻ ፍላጎት የተሰጠ ስለማይሆን የማስረጃው ተዓማኒነት ዝቅተኛ ስለሚሆን በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የተደረገበት አግባብ ከገለልተኝነትና ከማስረጃ ተዓማኒነት ጋር የተያዘዘ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ የተገለጸውን ስንመለከት የቃል መቀበል ስራ

---

[62] ዝኒ ከማሁ

[63] ዝኒ ከማሁ

[64] አባዬ ዳኜው፣ በፌደራልና በአማራ ክልል ከጠበቃና የህግ አማካሪ ጋር ግንቦት 11/2011 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ እንዲሁም ተስፋ አባተ፣ በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የአዲስ አበባ ቋሚ ምድብ አቃቤ ህግ ጋር ሚያዚያ 21/211 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ

[65] ዝኒ ከማሁ

[66] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58

የሚከናወነው የቅድመ ክስ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ማለትም የጊዜ ቀጠሮ፣ የዋስትናና የምርመራ ስራን ለመምራት የሚመራው ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ስለሆነ የኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ የህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግን እንደ ምንጭ የወሰደ በመሆኑ የኢትዮጵያ የወንጀልኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግም ተመሳሳይ አቋም በመያዝ የተቀረጸ ነው፡፡ ምክንያቱም ለፖሊስ የተሰጠው የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ ካልተደረገ የተገኘው ማስረጃ ገለልተኛና ተዓማኒ አይሆንም ከሚል እምነት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ያረቀቁት ባለሙያዎች አንቀጽ 35 ስር ያለውን ሲያስቀምጡ የህንድን የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አቀራረጽ የተከተለ ሊሆን እንደሚችል የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ያምናል፡፡ ምክንያቱም በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት በቃል መቀበል ወቅት በፍርድ ቤት የተሰጠው የእምነት ቃል ነው እንደ ማስረጃ የሚወሰደው፡፡ በፍርድ ቤቱ ፊት ያልተሰጠ እንደ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተመሳሳይ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግም በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ ተቀባይነት እንዳይኖረው በማሰብ አንቀጽ 35 የተቀረጸው በዚህ አመክንዮት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከትም በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 27(2) መሰረት የተሰጠ የእምነት ቃል በዚሁ ህግ በአንቀጽ 35 መሰረት ያልተረጋገጠ ከሆነ የእምነት ቃሉን ፍርድ ቤቶች እንደ ማስረጃ ቢቀበሉትም ለማስረጃው የሚሰጡት ክብደት ዝቅተኛ ነው፡፡[67] ለዚህም የሚቀርበው ምክንያት ማስረጃው በነጻነትና በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ነው ተብሎ ስለማይገመት ማስረጃው ገለልተኛ እና ያለምንም ጫና ያልተሰጠ ማስረጃ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸው በመገንዘብ ለማስረጃው የሚሰጠው ክብደትና ተዓማኒነት ዝቅተኛ ነው፡፡[68]

## 3.2 የተጠርጣሪ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ሳይፈጸሙ የተገኘ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ያለው ተቀባይነት

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ አላማ መርማሪ ፖሊሶች ማስረጃ በሚያሰባስቡበት ወቅት የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል ሲቀበሉ ማናቸውንም የሀይልና የማባባያ ዘዴዎች ከመጠቀም መታቀብን ጨምሮ የስነ-ስርዓት ህጉ ለተጠርጣሪው ያስቀመጣቸውን ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች መሰረት አድርጎ ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ እንደሆነ አይተናል፡፡ በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን ሀይል በመጠቀም ማስረጃ ለመሰብሰብ የሚደረገው ተግባር በማህበረሰቡም ሆነ በፍትህ አካሉ ዘንድ በእጅጉ የሚወገዝ ተግባር

[67] ዝኒ ከማሁ
[68] ዝኒ ከማሁ

እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል። ምንም እንኳን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ስራ ላይ ከዋለ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ቤት ያለው እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይገባል የሚለው አከራካሪ ጉዳይ ላይ መልስ የለውም። በዚህም ምክንያት በባለሙያዎች ዘንድ የተለያዩ ግንዛቤና በተግባርም የተለያዩ አሰራር እንደነበር ይታወሳል። አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉትና በተግባርም ሲሰሩ የነበረው ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በማስገደድና በሌሎች ተጽዕኖዎች የተገኘ ቢሆንም ማስረጃው ጉዳዩን ለማስረዳት ተጨባጭ እስከሆነ ድረስ ማስረጃውን በመቀበል መርማሪ ፖሊስ ለፈጸመው ተግባር በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ ይገባል በሚል ክርክር ማስረጃውን በመቀበል ውሳኔ ሲሰጡ እንደነበር ይታወቃል።[69] በሌላ በኩል ያሉ ባለሙያዎች እንደሚሉትና በተግባርም ሲሰሩ የነበረው በማስገደድና በሌሎች ዘዴዎች የተገኘን ማስረጃ ልንቀበል አይገባም፤ ማስረጃው የቱንም ያክል ለጉዳዩ ጠቃሚ ቢሆንም የውሸት የእምነት ቃሎች አንድም በማስገደድ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ተስፋ በመቁረጥ ወይም ከጭንቀት በመነጨ ምክንያት የተሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ተጠርጣሪዎቹ ከሚደርስባቸው ጫና ለመላቀቅ ሲሉ የሚሰጡት ቃል ሊሆን ይችላል።[70] ምክንያቱም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ክፍተት ቢኖርበትም ከአጠቃላይ ከማስረጃ ህግ አስተምህሮትና ልምድ በመነሳት በሀይል የተገኙ ማስረጃዎች እንዲሁም ከእምነት ቃሉ በመነሳት የተገኙ ሌሎች ማስረጃዎችም ውድቅ ሊደረጉ ይገባል ከሚል በመነሳት ነው።[71] ምክንያቱም የህገ-ወጥ ተግባር ፍሬ ነው ልክ የመርዛማ ዛፍ ፍሬዎች (Fruit of Poisonous Tree Doctrine) እንደሚባለው ዓይነት ስለሆነ ማስረጃዎችን ባለመቀበል በግልጽ ባይሆንም እንኳን ማስረጃውን ያለመቀበል አሰራር (The exclusionary rule) መርህን ተፈጻሚ የሚያደርጉበት እንደነበር እንረዳለን።[72] ይህንን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ይታይ የነበረውን ክፍተት የቀየረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ስራ ላይ መዋል ነው። ምክንያቱም በዚሁ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(5) ስር **"የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት አይኖረውም"** በማለት ያስቀምጣል። ከዚህ ድንጋጌ ስር በግልጽ እንደተመለከተው በማናቸውም ሁኔታ በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት እንደሌለው መገንዘብ ይቻላል።

---

[69] የወንጀል መዝገብ ቁጥር 236/59 በ Stanley Z. Fisher እንደተጠቀሰው፣ Ethiopian criminal procedure: A source Book, (Faculty of Law, HSIU, Addis Ababa, 1969) ገጽ 73 እንደተጠቀሰው
[70] ዝኒ ከማሁ
[71] የወንጀል መዝገብ ቁጥር 62/75 በንጋቱ ተስፋዬ እንደተጠቀሰው፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ማስተማሪያ (ያልታተመ) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት፣ 1990፣ ገጽ 193
[72] ዝኒ ከማሁ

ሌላው ከእምነት ቃል ጋር ተያይዞ የሚነሳውና በህጎቻችን በግልጽ ምላሽ ያልተቀመጠለት ጉዳይ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን በአንቀጽ 27(2) ስር እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር ዝም የማለት መብት እንዳለ ያስቀምጥና ይህን መብት በመተላለፍ የተገኘ ማስረጃ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው በግልጽ ተቀምጦ አለመገኘቱ ነው፡፡ እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች **"ዝም የማለት ያለመናገር መብትና የተናገረው ማንኛውም ቃል በፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ተደርጎ ሊቀርብ እንደሚችል"** የተገለጸው ነው፡፡ ይህ የሚደረግበት ሁኔታ ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት ያለው መሆኑን እንዲያውቅና የሚናገር ከሆነም መናገሩ ውጤት እንዳለው በቂ እውቀት እንዲኖረው በማድረግ የሚጠቅመውን አስቦ እንዲወስን ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህ መብቶች በግልጽና በሚገባው ቋንቋ ሊነገሩት እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ እነዚህ መብቶች እንዳሉት ካወቀ በኋላ በማወቅና በመገንዘብ ቃሉን ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ይወስናል ማለት ነው፡፡ ለተጠርጣሪው የተደረገው ጥበቃ ከዚህ ዓላማ የመነጨ ነው፡፡ ስለሆነም ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ተጠርጣሪው እነዚህ መብቶች ሳይነገሩት የእምነት ቃሉን የሰጠ ቢሆንና ዐቃቤ ህግም በማስረጃ ዝርዝር ውስጥ በማካተት በፍርድ ቤት ቢያቀርበው ተጠርጣሪው በበኩሉ ለፍርድ ቤቱ እነዚህ መብቶች ያሉኝ መሆኑ ሳይነገረኝ የሰጠሁት ቃል ስለሆነ ማስረጃው ሊያዝብኝ አይገባም የሚል አቤቱታ ቢያቀርብ ፍርድ ቤቱ በማስረጃው ተቀባይነት ላይ ምን ሊወስን ይችላል የሚለው አከራካሪ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት በባለሙያዎች ዘንድም የተለያዩ ግንዛቤ እንዳለና በተግባርም የተለያዩ ውሳኔ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው በስነ-ስርዓት ህጉ የተቀመጡት መብቶቹ በዝርዝርና በሚገባው አኳኋን ሳይነገረው ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጎ ከሆነና የእምነት ቃሉን ከሰጠ መብቶቹ ሳይነገሩት የተሰጠ ቃል ስለሆነ ውጤቱ ምን መሆን አለበት የሚለው በግልጽ ስላልተመለከተ ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ አይቻልም በሚል ይከራከራሉ፡፡[73] በሌላ በኩል ያሉ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው በህጉ የተደረጉለት ጥበቃዎች ሳይነገሩት የእምነት ቃል ሰጥቶ ከሆነና ይሄው ከተረጋገጠ ማስረጃው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ክርክር ያቀርባሉ፡፡ ለክርክራቸው ማጠናከሪያ የሚያደርጉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9 ስር የተመለከተውን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ *ይሄውም በዚህ ድንጋጌ በንኡስ ቁጥር 1 ስር ህገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ እንደሆነ ያስቀምጥና ማንኛውም ህግ፣* ልማዳዊ አሰራር፣ የየትኛውም ባለስልጣን ውሳኔ ይህን ህገ መንግስት የሚቃረን ከሆነ ውጤት

---

[73] በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሚሰሩ ዳኞች ጋር በ2010 ዓ.ም የተደረገ የጋራ ውይይት

እንደሌለው ያስቀምጣል። ይህ ማለት መርማሪ ፖሊስ የመንግስት አካል እንደመሆኑ መጠን አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃል ከመስጠቱ በፊት በህገ መንግስቱ ለተጠርጣሪ የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችን ተግባራዊ ሳያደርግ የተቀበለው የእምነት ቃል ህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን የሚቃረን ስለሆነ የተገኘው ማስረጃ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ከሚል መነሻ ነው። ከላይ የተቀመጠውን የህገ መንግስት ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቶች የተጠርጣሪው መብቶች ሳይገለጹ የተገኘ ማስረጃ ውቅድ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።[74] እንደ ጸሀፊው እምነት ከሆነ  በአንቀጽ 27(2) ስር ተጠርጣሪው የሚሰጠው ማንኛውም ቃል እንደ ማስረጃ ሊወሰድ የሚችል መሆኑ ሊነገረው ይገባል በማለት ያስቀምጣል። ይህን መብት መግለጹ ዋናው ምክንያት ተጠርጣሪው በመብቱ ላይ ለሚወሰደው እርምጃ ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ማለትም ቃል በመስጠቱና ባለመስጠቱ መካከል ሊኖር የሚችለውን ጉዳትና ጥቅም አገናዝቦ እንዲሰጥ ያደርገዋል በሚል ነው። ስለሆነም እዚህ ላይ መገንዘብ የሚቻለው መብቱን ለተጠርጣሪው መግለጽ የሚጠቅመው ለሚሰጠው ማስረጃ ተቀባይነት ወይም ተዓማኒነት መሰረታዊ መሆኑ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የተዘረጉት የእምነት ቃል በነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፍላጎት እንዲሰጥ ለማስቻል ነው። ይህ ካልተደረገ ግን አንድ ተጠርጣሪ ራሱን ያለመወንጀል መብቱን ከመጣሱም በላይ ተጠርጣሪው ያሉትን ህገ መንግስታዊ መብቶች በተለይም እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት ይጋፋል። ፍርድ ቤቶች እነዚህን ማስረጃዎች ውድቅ የማያደርጉ ከሆነ መርማሪ ፖሊሶች ሌላ ማስረጃ በተመሳሳይ መንገድ ለመሰብሰብ መንገዱን እንዲጠቀሙ ይገፋፋቸዋል፤ በሌላ አገላለጽ አሉታዊ/መጥፎ ማበረታቻ (bad incentive) በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

ሌላው ከእምነት ቃል ጋር በተያያዘ የሚነሳው ክርክር የተጠርጣሪው መብቶች ተነግረውት ነው የእምነት ቃሉን የሰጠው አይደለም የሚል ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን ማስረዳት ያለበት ማነው ነው የሚለው ነው። ይህንን በተመለከተ ሁለት ዓይነት ሀሳቦች ይቀርባሉ። አንዳንዶች እንደሚሉት የተሰጠው የእምነት ቃል ህጉ ያስቀመጠውን ስርዓት ተከትሎ መሆን አለመሆኑን ተጠርጣሪው እንዲያስረዳ ቢደረግ ተጠርጣሪው ቃሉን የሚሰጠው በጠባብ ክፍል ውስጥ እና ሰው በሌለበት ሁኔታ ስለሆነ ተጠርጣሪውን አስረዳ ማለት ምክንያታዊና አመክንዮታዊ ስላልሆነ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው መብቶቹ ተነግረውት መሆኑን መርማሪ ፖሊስ ሊያስረዳ ይገባል የሚል ክርክር የሚያቀርቡ አሉ።[75] እነዚሁ ባለሙያዎች ተጠርጣሪው በፍርሀትና ብዙ ጫናዎች ሊደርሱበት በሚችል ሁኔታና

[74] ዝኒ ከማሁ
[75] ዝኒ ከማሁ

ቦታ ውስጥ ሆኖ ቃሉን የሰጠ በመሆኑ መብቶቹ ሳይነገሩኝ ነው የሚለውን እንዲያስረዳ ቢደረግ ፍትሀዊ አይደለም በማለት ክርክራቸውን ያጠናክራሉ።[76] ይህንን ክርክር ለመመለስ በማሰብ አሁን አሁን በመርማሪ ፖሊሶች በኩል እየተለመደ የመጣው አሰራር ተጠርጣሪው በራሱ ፍላጎት ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ምስክሮች ናቸው በማለት የደረጃ ምስክር ሲቀርብ ይታያል። በእርግጥ የደረጃ ምስክር በህጉ ላይ የተቀመጠ ባይሆንም ዓላማው ተጠርጣሪው በነጻ ፍላጎቱና መብቶቹ ተነግረውት ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ለማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ አሰራሩ ብዙ ላይነቀፍ ይችላል። ይሁን እንጂ የደረጃ ምስክር በመሆን የሚቀርቡት ሰዎች ምርመራው በሚከናወንበት ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ/የሚሰሩ/ የፖሊስ አባላት ስለሆኑ ገለልተኛና ነጻ ሆነው ስለነበረው ነገር በአግባቡ ያስረዳሉን የሚለው ሌላ አከራካሪ ጉዳይ ነው። በእርግጥ ፍርድ ቤቶች አንድን ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃልን ምን ያክል በነጻ ፍላጎት የተሰጠ ነው የሚለውን ለመለካት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ቃል መቀበሉ የተከናወነበት ጊዜ፣ ቃል ለመቀበል የወሰደው የጊዜ ርዝማኔ፣ ቃል የመቀበል ስራው የተካሄደበት ቦታ፣ የተጠርጣሪው እድሜ እና ሌሎች መመዘኛዎችን ማየት ይገባቸዋል። ለምሳሌ በቃል መቀበያ ክፍል ውስጥ ሰው በሌለበት ሁኔታ ቃላቸውን እንዲሰጡ የሚደረጉ ተጠርጣሪዎች በሀሰት የእምነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ። በሌላ በኩል የእምነት ቃል በምን ሀሳብና ዓላማ ተሰጠ የሚለውም መታየት ይገባዋል። ይሄውም የተገኘው የእምነት ቃል ሀሰተኛ የእምነት ቃል እንዳይሆን ከሚፈጥሩ ስጋቶች ነጻ መሆን ይገባዋል። *አስገዳጅ በሆነ አካባቢ (ጠባብ ክፍል እና ሰው በሌለበት) የሚደረግ ቃል መቀበል በተፈጥሮው የተጠርጣሪውን እራስን ያለመወንጀል ነጻነት የሚጋፋ ወይም የሚጫን ነው።* የቃል መቀበሉ ጊዜ መርዘም፣ ቃል የተሰጠበት ቦታ እና ሌሎች ሁኔታዎች የማስገደድን ውጤት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ፍርድ ቤቶች እነዚህን አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ማየት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም የተጠርጣሪን የእምነት ቃል በሚመለከት የተጠርጣሪው የትምህርት ደረጃ፣ እድሜ እና ሌሎች ዙሪያ መለስ የሆኑ ጉዳዮችን ማየት ይገባል።

---

[76] ዝኒ ከማሁ

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በመሆን ከማስረጃ ሚዛን ውስጥ እንዲገባ ከተፈለገ ማስረጃው የተገኘበት አግባብ ህጋዊ መሆን ይገባዋል፡፡ ይሄውም የመጀመሪያው ነጥብ ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ያለምንም ተጽዕኖ መሆኑን መርማሪ ፖሊስ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ለተጠርጣሪው ይጠቅማሉ በሚል በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ የተቀመጡ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ማለትም ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ የሚናገረው ማናቸውም ቃል እንደ ማስረጃ በፍርድ ቤት ሊወሰድ የሚችል መሆኑ ለተጠርጣሪው በሚገባው ቋንቋና በግልጽ ተነግሮት የሰጠው ቃል መሆኑን ፖሊስ እንዲያረጋግጥ ማድረግ ይገባል፡፡ እነዚህ ከላይ የተቀመጡት መሰረታዊ ጉዳዮች ሳይከበሩ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆኖ ከቀረበ ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡